# <u>ወያኔ ማለት ምን ማለት ነው?</u>
# <u>ወያኔዎች እነማን ናቸው/ ምን ሰሩ ምን እያደረጉ ነው?</u>

ከቀመሩ ደሳለኝ

ወያኔ ብለው እራሳቸን የሚጠሩት ወያኔዎች ስር መነሻቸው በትግራይ ክፍለ ሀገር በተወሰኑ ሰዎችና ቦታዎች በጣሊያን ወረራ ጊዜ በጣሊያን አፍቃሪነት ፀረ-ኢትዮጵያ ሆነው ከጣሊያን ጎን ተሰለፈ ኢትዮጵያኖችን የወጉ ጉግ ማንጉግ፣ ከሃዲዎችና ሆዳም ከይሲ የወንበደዎች መጠሪ ስም ነበር-ነው።

የቃላቱ አመጣጥና ትርጉም ትግርኛ-አማርኛ መነሻ(root )ሲሆን "ወያኔ" ትርጉሙ ወየነ፣ወገነ፣ ሸፈተ፣ አመፅ፣እምቢአለ፣አጋሚዶ፣አረመኔ፣አታላይ፣ጨካኝ፣ቀማኛ፣ዘራፊ፣ሌባ፣ወራዳ፣ሥርዓት ሞራል የጎደለው፣ ሕግ የማያውቅና ሕግ-ወጥ፣ትዕዛዝ የማይቀበል፣ሊታዘዝና ሊመራ የማይችል ጋጠ-ወጥ፣ሞገደኛ፣ሥርዓት አልባ፣ማንዘራሽ፣ቅሌታምና ግልቱ የመሳሰሉት ትርጓሜ ያለው ሲሆን በአጠቃላይ ጋጠ-ወጥ፣ ወፍ ዘራሽ ስድ ዘራፊ ሥርዓት አልባ ወሮ-በላ ማለት ነው።

ይህ ባህሪ የተጠናዎታቸው አጋሚዶ፣ሌባና ዘራፊ ኃይሎች በጣሊያን ወረራ ጊዜ ኢትዮጵያን ክደው ከጣሊያን ጋር በመስማማትና በመተባበር ለጣሊያን አጋዥና ረዳት ሆነው የኢትዮጵያን ወታደራዊ ሰራዊት፣አርበኛውንና አገር ወዳድ ሕዝብ በእጅጉ የጐዱ፣ ያስቸገሩና ያሰቃዮ የፀረ-ኢትዮጵያ የነፃነት እንቅፋትና ከሃዲ ባንዳዎች የነበሩ ናቸው።በአምስት ዓመት የጣሊያን የወረራ ጊዜ እነዚህ የትግራይ ክፍለ-ሀገር ፀረ- ነፃነት ወንበደ-ሽፍታዎች፣የኢትዮጵያን ወታደር እየሰለሉ መረጃና ኢንፎርሜሽ ለጣሊያን ያቀብሉ ነበር። እየመሩና አቅጣጫ በማሳሳት መርተው በጠላት እጅ እንድያዙና እንድገደሉ፣ ከማድረግ ጋር እራሳቸውም በቀጥታ ይዋጓቸውና ይገሏቸው፣ስንቃቸውን ይቀሟቸው እንደ ነበር ታሪክ በስፋት መዝግቦታል። (**ቀይ አንበሳ፣ ያበሻ ጀብዱ ትርጉም መጻሃትና (Prevail)ፕሬቪል-እንግሊዘኛ**) አንብቡት።

የኢትዮጵያና የጣሊያን ጦርነት ሲጀመር አንስቶ የትግራ ባንዳ ወያኔዎች፣ የራያና አዘቦ አካባቢ ጣሊያን ይግዛን አትምጡብን፣ በቦታችን አታልፉም፣በዚህ አትኼዱምና አናስደርስም በማለት መንገድ በመዝጋት በጉድጓድ ውስጥና በዛፍ ላይ በመደበቅ ሳይታዮ ተኲሰው መግደል፣ መበታተንና ስንቅ፣ መሳሪያቸውን ይቀሙ ነበር።

ኢትዮጵያኖች አገራቸው በጣሊያን ፋሽስት ተወርሮ፣ ተዋግተው የአገር ነፃነትና ደህንነት ለማስከበር ከተለያዮ ቦታዎች በተለይም ከእሩቅ በሺዎች የሚቆጠሩ ዘምተው ሲመጡ ለምሳሌ(ከባሌ፣ ከጂማ፣ ከጎሞን-ጎፋ፣ከሲዳማ፣ወላይታ . . . ወዘተ) 900-1000 ኪሎሜትር በፀሐይ ሃሩርና በዝናብ፣ ቀን ከሌሊት 5—6 ወራት በእግር ተጉዘው የመጡ አገር ወዳድ ጀግና አርበኞች ጠላታቸውን ጣሊያንን ሳያዮና ጦርነት ሳይገጥሙ በራያና አዘቦ ባንዳና ሽፍታ እዛፍ ላይ ቁጭ ብለው ግንባር ግንባራቸውን እየመቱ በመግደል ትጥቅና ስንቃቸውን በመቀማት ኢትዮጵያዊ ወታደሮችን ይገሉና ያውኩ ነበር።አካላቸውን በመቆራረጥ፣ ብልታቸውን በመስለብ፣ የገደሉትን ቁጥር ብዛትና መሳሪያዎች ለጣሊያን ጀኔራሎች በማሳየትና በመሰጠት ይሾሙና ይሸለሙ ነበር።(ማንው ያንጊዜ ባንዳ ? ወያኔዎች አባቱ፣ አያቱ ፤ ዛሬ ልጆች ኢትዮጵያን በዝባዥ)።

በእንደዚህ ሁኔታ አገር አቋርጠው፣ሰንቀ የሸንብራ ቆሎ፣ ቂጣና በሶ አድርጐ፣ ከሩቅ የመጡ ኢትዮጵያዊ ጀግኖች፣ አርበኛች ጠላቱን ጣሊያንን ሳያዩ፣ሳያውቁና ሳይዋጉ፣ የእኔ ያለ ሰው፣ ኢትዮጵያዊ ናቸው ያላቸው ፣ሊረዳው የመጡለትን ጠላት በማድረግ ባንዳዎች ተደብቀው ገደሏቸው፣ ዘረፏቸው። (ገዳይ ባንዳ ወያኔ ፣ ሟች ተገዳይ ኢትዮጵያዊ የእኔና የአንተ አባት፣ እናትና አያቶች መሆናቸው ነው። ልብ በል ያገር ሰው)።

**የማይጨው ጦር**

በኢትዮጵያና በፋሽስት ጣሊያን መካከል ያለው ጦርነት እየተባባሰ መጣ። ብዙ ባንዳዎች ለጣሊያን እየሰለሉ መረጃዎችን ጠላት አቀበሉ ፣ የኢትዮጵያን ወታደር ይገላሉ ስንቅና ትጥቅ እያደፈጡ ይቀማሉ። የትግራይ ክፈለ ሀገር አስተዳዳሪ ኃይለ ስላሴ ጉግሳ ኢትዮጵያን ከዶ ከጣሊያን ጋር በመወገን የራሱ ወታደር በማዘጋጀት ህዝቡን በማስፈራራት፣በማስገደድ፣ ስኳር በመስጠትና በመደለል ኢትዮጵያዊ ወታደርን እንዳይቀበሉ፣ ውሃ እንዳይሰጡ፣ በቤታቸው ላይ የጣሊያንን እንጂ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓማ እንዳይሰቅሉና እንዳያውለበልቡ ሲያደርግ፣ ወታደር እያስለጠነ በድብቅ፣ ሌላም ጊዜ የኛዎችን በመምሰል ይሰልል ፣ የተሳሳተ መረጃና አቅጣጫ በመስጠት በጠላት ያስመታ፣ትጥቅ ያስፈታ ነበር። ውሃ ውስጥ መርዝ እየጨመሩ ኢትዮጵያዊ ወታደሮችን መርዘው ይገሉ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል።

በዚህ ሁኔታ በማይጨው ጦርነት ላይ ብዙ የጦር አዝማቾችና እንዲሁም አፄ ኃይለ ስላሴ የተከፈሉበት ትልቅ ጦርነት የተካሄደበት ቦታ፣ ብዙ ጀብዱና ድል በጣሊያን ላይ ልክ እንደ አደዋ ጦርነት ብዙ መሰዋዕትነት ተከፍሎ ኢትዮጵያኖች ጣሊያንን አንበርክከው ወደ ኋላ መልሰውና አሸንፈው ነበር።ዳሩ ግን <u>በጣሊያን ቅጥረኛች ትግራይ ባንዳ ወያኔዎች የሚመሩ ወንበደዎች ከኃላ ዞረው በማድፈጥና ተደብቆ በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጦርነት በመፍጠርና በመውጋት ድሉን ለወራሪው ፋሽስት ጠላት ለጣሊያን እድሆን አስደረጉ</u>።ከዚህም የተነሳ መልሶ ማጥቃት ስላልተቻለ፣ ኢትዮጵያኖች በንጉሱ አማካይነት ብዙ ከመከሩ በኃላ ወደ ኃላ አፈግፍገው ሃይላቸውን ማጎልበትና መልሶ መዋጋት እንጂ በአለው የሰውና ትጥቅ፣ በዚህ ብንቆይ እኛም ሞተን አገርን ለጠላትና ለባንዳዎች ማስረከብ ነው ብለ ወደ መሀል ሀገር መሄድ እንዳለበቸው ወሰኔ አደረጉ።

ባንዳ ወንበደዎች በጠላት በመታገዝ በባስ እጅግ ማዋከ፣ዘረፋና ግድያ በኢትዮጵያኖች ላይ ፈጸሙ። የአደዋዋን ጦር መርተው ድል ያስገኙት ሰመ ጥሩው ጀግና አርበኛ እራስ ሙሉጌታ ከነ ልጃቸውና ብዙዎች፣ በዛፍ ላይ በተደበቁ የራያና አዘቦ ሽፍታዎች ውንዝ ሲሻገሩ በጥይት ተመተው ወደቁ፣ ተገደሉ። ብዙዎች መመለሻ መንገድ በማጣትና በመታወክ በጥይት፣ በውሃ ጥምና በረሃብ አለቁ። በዚህ የባንዳዎች አሻጥርና ከጠላት ጐን ቆሞ መውጋት፣ የማይጨው ድል በባንዳዎች በመደናቀፍ የኢትዮጵያ-ጣሊያን ጦርነት ለ5 ዓመት የአርበኝነት ትግል ተዘዋውሮ በብዙ ያላሰለሰ ትግል ተካሂዶ ነፃነት ተገኘ።

ባንዳዎች ከጠላት ወራሪ ኃይል ከጣሊያን ጎን ቆመው በሚያሳፍር ሁኔታ አገራቸውንና ህዝባቸውን ሲውጉ ሲገሉ፣ በትግራይ መሬት ላይ መውጫ መግቢያ ሲነሱና ሲያሳጡ ፤ **ኢትዮጵያን የሚወዱና የሚረዱ፣ የሚያግዙና ነፃነት አፍቃሪዎች,፣ፍሽዝምን የሚቃወሙ በጦርነቱ የተካፈሉ እጅግ ብዙ አገሮችና ግለሰቦች ነበሩ።ብዙውን ታሪክ የጻፍት የውጭ አገር ሰዎች በግላቸው ለመርዳትና በጦርነቱ ተዋጊም አዋጊም በመሆን የረዱ ናቸው።ብዙ የአፍሪካ አገሮች በሰው ፣ በቆሳቁስ፣ በአካል ተገኝተው ህይወታቸውን ለኢትዮጵያ መሬት ሰጥተዋል።የአፍሪካ አገር በአውሮፓ ተማሪዎች ተሰባስበው በመደራጀት እጅግ ከፍተኛ**

**አስተዋፅዖ አድርገዋል፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ ከፍ አርገው ለዓለም አሳይተዋል።(ለምሳሌ ጆሞ ኬኒያታ ይጠቀሳሉ)። ጥቁር አሜርካኖች ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት የፈቃደኛ ቢሮ ሃርለም ውስጥ ከፍተው ሰርተዋል፣ ብላክ ኢግልስ ከነ አይሮፕላናቸው ኢትዮጵያ ገብተው አገልግለዋል።ከተለያዩ የውጭ አገሮች ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ከኢትዮጵያኖች ጎን ሲቆስሉና ሲሞቱ ነበር።**

ነገር ግን <u>በኢትዮያ መሬት የተወለዱና ኢትዮጵዊ የሚባሉ ከፋሽስት ጣሊያን ጎን ቆመው ኢትዮጵያውያንን ወጉ- ገደሉ፣ አቆሰሉ፣ ስንቅ ዘረፉ አገር ሸጡ። ኢትዮጵያንና ወንድሙን ለስኳር ለወጠው ገደሉ</u>።የራያና አዘቦ ሽፍታዎች ተደብቀው ኢትዮጵያኖችን የሚገሉ፣ ይደስቱና ለድላቸው ምልክት ብልቱን ሰልበው ይዘው ይሄዳሉ።እነዚህ ሽፍቶች ንጉሱንም እግዚአብሔርንም አያውቁም።በጣሊያን ስካር የሚታለሉና አገራቸውን የሸጡ በበንዳዎች በነ ኃይለሰላሴ ጉግሳ፣ በመለስ ዜናዊ አያት ባንዳው ዓይነት የሚመሩ ነበሩ። ኢትዮጵያ ፋሽስት ጣሊያንን አይቀጡ ቅጣት ሰጠች።ጣሊያን ተፈጸመ፣ ኢትዮጵያ እንዳይደርስ ሆኖ ተሸነፈ! !

ከ5 ዓመት የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ፅኑ፣ቆራጥ፣መራራ፣ከባድና ትልቅ መስዋዕትነት በኢትዮጵያዊነት ትግል ጣሊያን ተሸነፈች ኢትዮጵያ ማንነቷንና ነፃነቷን አረጋገጠች።
በጣሊያን ድል መነሳት ባንዳዎች፣ የራያና አዘቦ ወንበደ ሽፍታዎች እጅግ ተከፉ፣ ጣሊያንን እንፈልጋለን፣ በጣሊያን መገዛት ነው የምንፈልገው በማለት፣ ለኢትዮጵያ መንግሥት አንገዛም፣ አንታዘዝምና አንገብርም ብለው "ወየኑ" አጋሚዶች፣ሽፍቶች፣ ወያኔዎች ሆነው በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ አመፅ።ወያኔዎች በሚል ስም ስያሜ እየተጠሩና ችግር በመፍጠራቸው የኢትዮጵያ መንግሥት አስፈላጊውን እርምጃ በማድረግና ትምህርት በመስጠት ሰጥ ለጥ ብለው እንድገዙ ተደረገ። **<u>ይህ አንደኛው ወይም የመጀመሪው ወያኔ ነበር።</u>**

<u>እነማናቸው ወያኔዎች?</u>

የዚህ ያንደኛውን ወያኔ መሰል ባህሪና ተግባር ያላቸው ቅሪተ -ሃሳብ የያዙና ከአባት- ከአያቶቻቸው የተማሩትንና የወረሱትን ልክ እንደ አንደኛ **ወያኔ ከ40 ዓመታት በኃላ የባንዳ ልጆች በመሰባሰብ ፀንሰው፣ በለስ ቀንቷቸው ኢትዮጵያን በጠብመኝ ሃይል ይዘው፣ እየገዙ ያሉት ሁሉም በአባቱ ወይ በእናቱ ወገን አያቶቻቸው ባንዳዎች ፣የጣሊያን አሽከር ፣ ለሆዱ አገር ወገን የከዳ፣ የሸጡ ቅሌታምና የተራ ሰዎች ልጆች <u>እነዚህ ዛሬ ኢትዮጵያን ወረሮ ህዝብና አገር እያጠፉ ያሉት ሁለተኛው ወያኔዎች -አሸባሪዎች ናቸው።</u> "ወያኔ" ብለው እራሳቸውን በመጥራት የተነሳሱት(2 ኛው)፣ አያቶቻቸው የኢትዮጵያን ጀግና አርበኛ ገለው በሬሳው ላይ እግሩን ጭኖ ፎቶግራፍ በመነሳት ለሙሶሎኒ ጀኔራሎች በመላክና በማቅረብ ይሾሙ ይሸለሙ የነበሩ ባንዳዎች፣ ዘመዳሞች ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው።** ለምሳሌ የመለስ ዜናዊ አያት ዋና ባንዳ የነበረና ጣሊያን ደጃዝማች ያለው ሲሆን የትግራይ ኢትዮጵያዊ ህዝብ የጠላው፣ ሲሞት እንኳን መቀበሪ ቦታ የተከለከለውና ከመንገድ ዳር የተቀበረ ነበር።በዚህ ሁኔታ ዛሬ አገራችንን የሚጫወቱባት አሸባሪዎች 18—20 በዋናነት በስልጣን ላይ ያሉት የባንዳ የልጅ ልጆች ባንዳዎች ናቸው።በሚድያ በኩል ብንመለከት ኢትዮ-ሚድያን በባለቤትነት ይዞ ወያኔን የሚቃወም ጹሁፍ ሲጻፍ የማያወጣው አብረሃ በላይ አያቱ ባንዳ ነበር።ተቃዋሚነኝ የሚለው ግንቦት 7 የባንዳ ዋሻ ነው።ድርጅቱ እንዳለ የሻቢያ ቅጥረኛ ባንዳ ነው። ሻ/ቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ አባቱ የጣሊያን ባንዳ፣ እሱ እራሱ የወያኔና የሻቢያ ባንዳ ነው። ከሳ ከበደም እንደዚሁ ባንዳ ኢትዮጵያኖችን(አማራ) ፈላሻ ብሎ በገንዘብ ለእስራኤል አሳልፎ የሰጠ የሸጠ ባንዳ ነው። <u>ሦሥተኛው ወያኔ ደግሞ ከሁለተኛው ወያኔ ተባረው የወጡት ያቋቋሙት አራና እየተባለ የሚጠራው በነ ገብሩ አስራት የሚመራው እንደሆነ አትዘንጉት።</u>

ስለዚህ ሁሉን አውቆና ለይቶ መረዳት አቋምና ትግልን አቅጣጫ ይሰጣል። ከእያንዳንዳችን ኢትዮጵያኖች አያቶቻችን ቢያንስ አንድ ሰው በጣሊያን ጦርነት ለኢትዮጵያ ነፃነት ሞቶብናል።ዛሬም በባንዳ ልጆች እየተገደልን ይባስ ብሎ ማንነትህ ተዋርዶና ተገፈህ የመሬት ባለቤትነት ተነጥቀህ፣ ዜግነት የሌለህ በአገሪቱ መኖር ተነፍጐህ በመሰደድ እየሞትክ፣ አገሪቱም ለባዕዳን እየተሸጠች ነው ያለህ። በዙሪያህ ያለው ባንዳና የባንዳ ልጆች፣የባንዳ ቅጥረኞች ናቸው።
ከዚህ በላይ ከታሪክ አጣቅሸ እንዳቀረብኩት ወያኔ ምን ማለት፣ የወያኔ ባንዳዎች ባህሪና ተግባር በአጭሩ ያስገነዝባል፣ መረዳትና ወደ ተግባር መቀየር ያንተ ፈንታ ነው።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !**

*ዛሬ አገራችንን ኢትዮጵያን ለሁሉት ከፍለው፣ ቀሪውን በክልል ውስነውና ገድባው መሬት የአንተ አይደለም በማለት እነሱ እየሸጡት፣ አንተ እየተረሀብክ ፣እየተሰደድህ፣ መከራ ስቃይ እየደረሰብህ ለ25 ዓመታት ከፋፍለውና አዳክመው፣ አለያይተውና አናክሰው እየገዙህ ሲሆን አንተም ዝም ብለህ ከመገዛትም አልፈህ ዝም ብለህ እየተገዛህና እየሞትክ የወደፊቱን ትውልድና አገር ከጠላቶችህ ጋር ሳታውቀው ተባብረህ እየበደልክና እየገደልክ ነው።*

*ያንተ ቀደምት ትውልድ ሞተው፣ ደም አፍሰው ፣ አጥንት ከስክሰው ያቆዩልህን ነፃ አገር ባንዳ የባንዳ ልጆች በወንበደነት አባቱና አያቱ፣ ያንተን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ጀግና አያት-ቅድመ አያቶችን የገደሉ ሲሆን፣ነግር ግን ዛሬ የገደሉት ጌታህ ሆነው እንዲገዙህ ፈቀድህላቸ፣ ዝም ብለህ ትገዛለህ፣ በጠላትነት የሰሩትን መንገድ ተከትለህ ትሄዳለህ፣ ጉድጓድም ትገባለህ፣ ይገሉሃል ትገደላለህ አታንገራግርም። ምንድን ነው ጉዱ?*

*መቼ ነው ባንዳን ያጠፉውን፣ ገዳይህንና አስገዳዩን የምትለየው? መቼ ነው ማወቅና መረዳት የምትችለው? መቼ ነው ያወቀው ወገንህ ሲነግርህ መስማትና መረዳት መተገበር የምትችለው? መቼ ነው ታሪክህን አውቀህ እኔነትንህ በአንድ ኢትዮጵያዊነት የመትጠብቀው? መቼ ነው ለመብትህ ፣ለአገርህና ለትወልድ የምትሆነው?መቼ ነው ታግለህ ነፃ የምትውጣው?*

**ኢትዮጵያዊ ሆይ!** *ሰው በስራ፣ በተግባር ይተረጐማል።ሰው፣ሰው ለመሆኑ የሚነግርና የሚገልጽ ሥራዎችን ሰርቶ በዚህ ቦታ በዚህ ዘመንና ወቅት ነበርኩ የሚሉ ቅሪት ነገሮችን ሰርቶና ጥሎ ያልፋል። ማንነቱን ለሚቀጥለው ትውልድ ማስረጃ ትቶ ይሄዳል።ይህ የሰውን ልጅ ከእንሰሳ የሚለየው አንዱ ባህሪ ነው።ሰለሆነም እኛ ኢትዮጵያኖች፤ ከየት እንደመጠን(ማንነታችን) የት እንዳለን፣ ወዴት መሄድ እንዳለብ ማወቅና መረዳት ግንዛቤም ውስጥ አስገብተን ማንነታችንን በርግጠኝነት ልንቀርጸውና ልናረጋግጠው ይገባናል።*

## ኢትዮጵያዊነትን ማወቅ ማንነትን ያረጋግጣል ! ! !

## ድል ለጭቁን ሕዝብ የእግዚአብሔር ፍትህ ! ! !